የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)
Ethiopian People's Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

# ሰያሚያችን ኢወክንድ
# ልሣናችን ነቅንቅ

**ልዩ መግለጫ** **ታህሳስ 2 ቀን 2002 ዓ.ም.**

## ወጣት ሰማዕታቶቻችን ሲታሰቡ

የኢሕአፓ የወጣቱ ክንፍ ድርጅት ስለሆንን ብቻ አይደለም ወክንድን መጠሪያችን ያደርግነው፤ የሕዝባችንን ነፃነትና የሀገራችንን ክብር አስመላሽ ክንድ መሆናችንን ለመግለጽ ፈልገን እንጂ።

ላይ ታቹ በወጣቶቻችን ደም የረሰርሰውን አካይስት የወያኔ ሥርዓት ካልተነቃነቀ አይነቀልም ለማለት ፈልገን ነው ልሳናችንን ነቅንቅ ብለን የሰየምነው።

እንደኮንጎዎች ደም በምስራቅ ከተሞች
ሁሌ እንደሚፈሰው
የሲዳማን መሬት ሻኪሶን ከተማ የኛዎቹ አራሰው።

የወጡና የገቡ፤ያለፉና የሚያልፉት አምባገነን የኢትዮጵያ ሥርዓቶች ለአንደበታቸው የመከፈቻ ዴሞክራሲያን ያደርጉና በምላሳቸው ደሞክራሲን ያንቀረቆሩና ደም የለመደው የፈሪ ጣታቸው ደግሞ ቃታ ይስብና የሕዝብ ልጆችን ደም ያንቀረቁራል።

በተለይ በአይናችን እያየነው ያለነው ሐቅ ይህ በመተፎ ሽታ ከርፍቶ የሚገኘው የወያኔ ሥርዓት ፍርሃቱ ልኬታ የለውምና ከሕዝብ በኩል ሆ የሚል የተባበረ ድምፅ በሰማ ቁጥር አካላቱ መረስረሱን ለመሸፋፈንና የፍርሃት ቆፈኑን ለመደበቅ የተኩስ እሩምታ ባልታጠቁ ወጣቶች ላይ በመርጨት ሊጀግን ይሞክራል።

የሚያስብ ጭንቅላት ይዞ አልተፈጠረምና ለሀገር የሚያስቡ ወጣቶችን ፣ የድሃ ልጆችን በጥይት አረር ያቃጥላል።
ዛሬ "እቡዬ ዜናዊ ኢትዮጵያዬ" የሚል የለበጣ ቅላጼ ከመጀመሩ በፊት የዛሬ 17 ዓመት የኮሌጅ ለጋዎች ኢትዮጵያ አትከፈልም በማለታቸው ብቻ ነበር በወያኔ ጉጅሌዎች በወርሃዊ ታህሳስ በሳንጃ የታረዱት።

በ 1991 ዓ.ም. ዴሞክራሲ ለሕዝብ ያሉትን የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን የዚሁ ቀፎ ሥርዓት ታጣቂዎች ተኩስ ከፍተው የ6 ኪሎን አደባባይ በታህሳስ የገና ዋዜማ ደም ያጠጡት ። በ91፤በ92፤ በ93 እያልን በወያኔ ሰለባ የሆኑትን አፍላ ችግኝ ወጣቶቻችንን መዘርዘር ብንጀምር ማለቂያ የለውምና በቱ ይቁጠረው ማለት ብንችልም የእነዚህን በልባችን ማህተም የሆኑ ሰማዕቶቻችንን ፈልግ ተከታዮች በርግጥም ክንዳቸው ነንና በጽኑ ቁርጠን ሥርዓቱን ለማድቀቅ መዘጋጀታችንን በሠማዕቶቻችን ደም ቃል እንገባለን።

የዚህ መግለጫ ጭብጡ የኢትዮጵያ አንጡራ ሃብት በአላሙዲና በወዲዜናዊ ኩብንያዎች ኢትዮጵያ አትመዘብርም ባሉ የደቡብ ኢትዮጵያ ወጣት የሻኪሶ ትንታጎች የረሸነውን የወያኔን አራጅ ቡድን ከፋኛ ለመኮንን ይሆናል።

የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት የሻኪሶ ወጣቶች ግድያ ትንሳኤ ለኢትዮጵያ ነውና በሀገር ፍቅር የነደደውን በወያኔ ጥይት የሞቀውን አካላታቸውን ለመንፈሳችን ብርታት ለትግላችን ነዳጅነት ብንጠቀምበት እንደማጠኑብን በኩራት እንገልጻለን።

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com